ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

Federal Civil Service Commission

# የመንግስት ተሿሚዎች የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1109/2018

መስከረም 2018 ዓ/ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በሥራ ላይ ያለው የመንግስት ተሿሚዎች የቀን የውሎ አበል ተመን በስራ ላይ ከዋለ ከአሥራ ሁለት ዓመታት በላይ ያስቆጠረ በመሆኑ፣

በአሁኑ ወቅት በክልሎች፣ በዞንና በወረዳ ከተሞች የሚገኙ ሆቴሎች ከሚያስከፍሉት የምግብና የመኝታ ዋጋ ጋር ሊመጣጠን ባለመቻሉ፣

ለመስክ ሥራ በሚወጡ ተሿሚዎች ላይ ከፍተኛ የወጪ ጫና በማሳደር በመስክ ስራ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳረፉም በላይ የሥራ ተነሳሽነትን በመቀነስ ለቅሬታና አቤቱታ ምክንያት በመሆኑ፣

በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (4) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአበል ዓይነቶችንና ክፍያዎችን እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈፃፀማቸውን ይከታተላል በሚል በመደንገጉ፣

ኮሚሽኑ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 አንቀጽ 156(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግስት ተሿሚዎች የሀገር ውስጥ የቀን ውሎ ክፍያ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1109/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አዋጅ"** ማለት የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 ሲሆን በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህም መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2) **"ደንብ"** ማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 502/2014 ነው፡፡
3) **"ኮሚሽን"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ተግባርና ሃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የተቋቋመው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነው፡፡
4) **"የቀን ውሎ አበል"** ማለት አንድ የመንግሥት ተሿሚ በአገር ውስጥ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ወደ ሆነ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ በዕለቱ ለመመለስ ሳይችል ሲቀር ለ24 ሰዓት ለሚያስፈልገው የምግብ እና የመኝታ ወጪ የሚከፈል አበል ነው፡፡
5) **"የውሎ ገብ አበል"** ማለት አንድ የመንግሥት ተሿሚ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጪ ወደ ሆነ ሌላ የሥራ ቦታ ሄዶ ዕለቱን የሚመለስ ከሆነ ለምግብ ለሚያስፈልገው ወጪ የሚከፈል አበል ነው።
6) **በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-**

**በፌዴራል ደረጃ**:

1) **የበላይ ሀላፊዎች** በሚለው ስር የሚካተቱት ምክትል ጠ/ሚኒስቴር፣ ሚኒስትሮች፣ የህዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎችና ም/አፈጉባኤዎች፣ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንትና ም/ፕሬዘዳንት፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ በሚኒስትርና ሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ ያሉ ተሿሚዎች፣ ኮሚሽነርና ም/ኮሚሽነሮች እና በነዚህ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣናት፤

2) **ከፍተኛ ሀላፊዎች** በሚለው ስር የሚካተቱት በፌዴራል ደረጃ ያሉ ኤጀንሲዎች፣ ባለሥልጣኖችና ኢንስቲትዩቶች ዋና ዳይሬክተሮችና ም/ዋና ዳይሬክተሮች፣ የጽ/ቤት ሃለፊዎችና ም/ሀላፊዎች፣ የፌዴራል ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት፣ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንቶችና ም/ፕሬዘዳንቶች ፣ አምባሳደሮች፣ እና በነዚህ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣናት፣

**በክልሎች ደረጃ**

1) **የበላይ ሀላፊዎች** በሚለው ስር የሚካተቱት የክልል ር/መስተዳድርና ምክትል ር/መስተዳድር (ፕሬዘዳንትና ም/ፕሬዘዳንት) የክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎችና ም/አፈጉባኤዎች፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንትና ም/ፕሬዘዳንት፣ የክልል መስተዳድር የካቢኔ አባላት፣ የአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ እስተዳደር ከንቲባና ም/ከንቲባዎች፣ የአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የካቢኔ አባላት፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪዎች እና በነዚህ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣናት፤

2) **ከፍተኛ ሀላፊዎች** በሚለው ስር የሚካተቱት የክልል ቢሮ ምክትል ሀላዎች፣ የአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የቢሮ ምክትል ሀላዎች፣ በክልል ደረጃ ያሉ ኤጀንሲዎች፣ ባለሥልጣኖችና ኢንስቲትዩቶች ዋና ዳይሬክተሮችና ም/ዋና ዳይሬክተሮች፣ በክልል ደረጃ የጽ/ቤት ሃለፊዎችና ም/ሀላፊዎች፣ የዞን ምክትል አስተዳዳሪዎች፣ የአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ስራ አስኪያጆች እና በነዚህ ደረጃ የተሾሙ ባለስልጣናት፤

3) **የክልል ምክር ቤት አባላት** በሚለው ስር የሚካተቱት የክልሎች የምክር ቤት አባላት፣ የብሄረሰብ ዞኖች ምክር ቤት አባላት ናቸው፡፡(የክልል ምክብር ቤት አባላት አንድ)፤

4) **የወረዳ ምክር ቤት አባላት** በሚለው ስር የሚካተቱት በክልሎች ያሉ የወረዳ የምክር ቤት አባላት እና የልዩ ወረዳ ምክር ቤት አባላት (የክልል ምክር ቤት አባለት ሁለት)፤

5) **መካከለኛ ኃላፊዎች** በሚለው ስር የሚካተቱት የዞን መምሪያ ሀላፊዎችና ም/ሀላፊዎች፣ የወረዳ አስተዳደሪና ም/አስተዳዳሪዎች፣ ወረዳ ጽ/ቤት ሀላፊዎችና ም/ሀላፊዎች፣ በክልሎች የከተማ አስተዳደር በሆኑ ከተሞች ወርሃዊ ደመወዝ ያላቸው የቀበሌ አመራሮች እና በነዚህ ደረጃ የተሾሙ የስራ ኃላፊዎች፣

6) **ሌሎች** በሚለው ስር የሚካተቱት ደመወዝ የማይከፈላቸው የቀበሌ ተሿሚዎች፣ የመንግስት ተቀጣሪና ተሿሚ ያልሆኑ ግለሰቦች፣ ደመወዝ የማይከፈላቸው የቀበሌ

አመራሮች አርሶአደሮች፣ ነጋዴዎች፣ የከተማ ነዋሪዎች፣ ተማሪዎች እና ተመሳሳይ የሆኑ ግለሰቦች ናቸው፡፡

## 3. ዓላማ

የመንግስት ተሿሚዎች የቀን የውሎ አበል ከወቅቱ የገበያ ዋጋ አንጻር ወጪን ለመሸፈን ያላስቻለ በመሆኑና ከፌዴራልና ከክልል የመንግስት ተቋማት አበሉ እንዲሻሻል ተደጋጋሚ ጥያቄ በማቅረባቸው ምክንያት የቀን የውሎ አበል ተመኑን ለማሻሻል በማስፈለጉ ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌዴራልና በክልል እስከ ቀበሌ አስተዳደር እርከን ድረስ የሚገኙ የመንግስት ተሿሚዎች የሚሸፍን ይሆናል ፡፡

## 5. የጾታ አገላለጽ

በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ላይ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም

## 6. የቀን ዉሎ አበል አተማመንና አከፋፈል

1. የተሿሚዎችና የህዝብ ተመራጮች የቀን ውሎ አበል ተመን የተመሠረተው ከሙሉ የአንድ ቀን የውሎ አበል ተመን ውስጥ 10% ለቁርስ፣ 25% ለምሣ፣ 25% ለእራትና እና 40% ለአልጋ በመመደብ ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት ተሿሚዎች እና የህዝብ ተመራጮች የምግብ አበላቸው ወይም 60% የተባለዉ በየሰንጠረዡ የተቀመጠዉ የሚከፈላቸዉ ሲሆን የአልጋ ወጪያቸው እንደ ምድባቸው በደረሰኝ ወይም በቁርጥ የሚከፈል ይሆናል።
2. የተሿሚዎች የቀን ውሎ አበል ተሿሚው ከመደበኛው ሥራ ቦታው ውጭ ለሥራ ጉዳይ ሂዶ ዕለቱን ካልተመለሰ በስራ ላይ ለሚቆይባቸው ቀናት ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራትና ለመኝታ ባረፈባቸው ቦታዎች ላይ ለክልል ከተማ፣ ለዞን ከተማ፣ ለወረዳና ማዘጋጃ ቤት በቦታው ላይ ተመስርቶ የተጠናው ውሎ አበል ለእያንዳንዱ ቀን፡ የሚከፈል ይሆናል

ሀ) ለክልል ዋና ከተማ የተመደበው ከታች በሠንጠረዥ 1 የተመለከተው፣

**ሠንጠረዥ 1፡ ለክልል ዋና ከተሞች እና የከተማ መስተዳድሮች የቀን ውሎ አበል ክፍያ የአበል መጠን**

| ተ.ቁ | ክልል | ለበላይ ኃላፊዎች | ለከፍተኛ ኃላፊዎች | ለምክር ቤት አባላት | | ለመካከለኛ ኃላፊዎች | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | I | II | | |
| 1 | አማራ | 1242 | 1035 | 1617 | 1365 | እንደ ደመወዛቸው መጠን በተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መጠን መሰረት ይከፈላል | 1204 |
| 2 | አዳማ ከተማ | 1296 | 1071 | 1607 | 1386 | | 1236 |
| 3 | ደቡብ ኢትዮጵያ | 1269 | 1062 | 1670 | 1418 | | 1257 |
| 4 | አዲስ አበባ | 1359 | 1035 | 2534 | 1922 | | 1638 |
| 5 | ሲዳማ | 1269 | 1062 | 1670 | 1418 | | 1257 |
| 6 | ቤንሻንጉል | 900 | 774 | 1456 | 1285 | | 1148 |
| 7 | ጋምቤላ | 1017 | 810 | 1467 | 1285 | | 1145 |
| 8 | ሐረር | 1098 | 927 | 1628 | 1425 | | 1278 |
| 9 | ሱማሌ | 1071 | 927 | 1414 | 1236 | | 1099 |
| 10 | አፋር | 1035 | 963 | 1446 | 1264 | | 1103 |
| 11 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 1269 | 1062 | 1670 | 1418 | | 1257 |
| 12 | ድሬ ዳዋ | 1233 | 972 | 1628 | 1428 | | 1285 |
| 13 | ትግራይ | 1170 | 927 | 1638 | 1383 | | 1218 |
| 14 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 1269 | 1062 | 1670 | 1418 | | 1257 |

ለ) ለዞን ዋና ከተማ በየክልሉ ለዞን ዋና ከተሞች የተመደበው ከታች በሠንጠረዥ 2 የተመለከተው፤

## ሠንጠረዥ 2፡ ለዞን ከተሞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ መጠን

| ተ.ቁ | ክልል | ለበላይ ኃላፊዎች | ለከፍተኛ ኃላፊዎች | ለምክር ቤት አባላት | | ለመካከለኛ ኃላፊዎች | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | I | II | | |
| 1 | አማራ | 1058 | 783 | 1432 | 1145 | እንደ ደመወዛቸው መጠን በተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መጠን መሰረት ይከፈላል | 970 |
| 2 | ኦሮሚያ | 1017 | 765 | 1407 | 1218 | | 1078 |
| 3 | ደቡብ ኢትዮጵያ | 729 | 639 | 1341 | 1138 | | 991 |
| 4 | አዲስ አበባ | | | - | - | | - |
| 5 | ሲዳማ | 729 | 639 | 1341 | 1138 | | 991 |
| 6 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 639 | 549 | 1281 | 1089 | | 945 |
| 7 | ጋምቤላ | 720 | 621 | 1355 | 1131 | | 977 |
| 8 | ሀረሪ | | 0 | 0 | 0 | | - |
| 9 | ሶማሌ | 666 | 585 | 1323 | 1078 | | 917 |
| 10 | አፋር | 990 | 756 | 1348 | 1127 | | 991 |
| 11 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 666 | 576 | 1341 | 1138 | | 991 |
| 12 | ድሬ ዳዋ | - | | - | - | | - |
| 13 | ትግራይ | 918 | 576 | 1460 | 1155 | | 977 |
| 14 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 729 | 639 | 1341 | 1138 | | 991 |

ሐ) የወረዳ ከተሞች፣ የማዘጋጃ ቤት ከተሞች እና የገጠር ቀበሌ የአበል መጠን በሠንጠረዥ 3 የተመለከተው ይከፈላል።

**ሠንጠረዥ 3፡ የወረዳ ከተሞች፣ የማዘጋጃ ቤት ከተሞች እና የገጠር ቀበሌ የአበል መጠን**

| ተ.ቁ | ክልል | ለበላይ ኃላፊዎች | ለከፍተኛ ኃላፊዎች | የምክር ቤት አባላት | | ለመካከለኛ ኃላፊዎች | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | I | II | | |
| 1 | አማራ | 608 | 608 | 1190 | 1022 | እንደ ደመወዛቸው መጠን በተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መጠን መሰረት ይከፈላል | 889 |
| 2 | ኦሮሚያ | 616 | 616 | 1271 | 1054 | | 907 |
| 3 | ደቡብ ኢትዮጵያ | 616 | 616 | 1187 | 1008 | | 872 |
| 4 | አዲስ አበባ | | | | | | |
| 5 | ሲዳማ | 616 | 616 | 1187 | 1008 | | 872 |
| 6 | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 540 | 540 | 1061 | 931 | | 809 |
| 7 | ጋምቤላ | 508 | 508 | 1148 | 959 | | 819 |
| 8 | ሀረሪ | | | | | | |
| 9 | ሶማሌ | 450 | 450 | 1131 | 963 | | 830 |
| 10 | አፋር | 608 | 608 | 1236 | 1026 | | 879 |
| 11 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 616 | 616 | 1187 | 1008 | | 872 |
| 12 | ድሬ ዳዋ | | | | | | |
| 13 | ትግራይ | 587 | 587 | 1250 | 1176 | | 935 |
| 14 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 616 | 616 | 1187 | 1008 | | 872 |

3. በፌዴራል ሆነ በክልሎች **የበላይ እና ከፍተኛ ኃላፊ** በሚል ትርጓሜ ወስጥ ለተካተቱት ብቻ የመንግስት ተሿሚዎቹ እስከ 4 ኮከብ ደረጃ ባለው ሆቴል የመኝታ ወጪ በሚቀርበው ደረሰኝ መሠረት ይሸፈናል።
4. በፌዴራል ሆነ በክልሎች **የበላይ ኃላፊ** በሚል ትርጓሜ ወስጥ ለተካተቱት ብቻ የመንግስት ተሿሚዎቹ ጋር ልዩ ጥበቃዎችና ሹፌር አብረዋቸው የሚጓዙ በመሆኑና ለበላይ ኃላፊዎቹ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ከበላይ ኃላፊዎቹ ተለይተው መንቀሳቀስ ስለማይችሉ እነዚህ አካላት የቀን የምግብ አበል በደመወዛቸው መጠን በተሻሻለው በመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል

መሠረት ከውሎ አበል መጠኑ ለምግብ የተተመነውን 60 በመቶ እየተከፈላቸው የመኝታ ወጪያቸው ግን የበላይ ኃላፊዎቹ በሚያርፉበት ሆቴል የባለ አንድ አልጋ ክፍል የመኝታ ወጪ በሚቀርበው ደረሰኝ መሠረት እንዲሸፈን ይደረጋል።

5. **"ለመካከለኛ አመራሮች"** በደመወዝ ስኬላቸው መሰረት የመንግስት ሠራተኛውን የቀን ውሎ አበል መጠን ይከፈላቸዋል።
6. **"ለክልል ምክር ቤት አባላት"** እና **"ሌሎች"** በሚለው ስር ለተመደቡ ተሿሚዎችና የህዝብ ተመራጮች ደግሞ የመንግስት ሠራተኛውን የቀን ውሎ አበል መጠን እንዲያገኙ ተወስኗል። በዚህም **መሠረት "ለክልልና ለዞን ምክር ቤት አባላት"** ለመንግስት ሠራተኞች የተፈቀደው የደረጃ ሶስት የቀን ውሎ አበል፣ **"ለወረዳ ምክር ቤት አባላት"** ለመንግስት ሠራተኞች የተፈቀደውን የደረጃ ሁለት የቀን ውሎ እና **"ሌሎች"** ለሚለው ምድብ ስር ለሚገኙት ደግሞ የደረጃ አንድ ምድብ የሠራተኞች የአበል መጠን የሚከፈል ይሆናል፡፡
7. ለምክርቤት አባላት፣ ለመካከለኛ አመራሮች እና "ሌሎች" ምድብ ላይ ላሉ ወደ ገጠር ቀበሌ ለስራ ሲሰማሩ ያለ ልዩነት 200 ብር እንዲከፈል ተወስኗል፡፡
8. አንዳንድ የክልል ከተሞች እና የዞን ከተሞች የወረዳ ከተማ መቀመጫዎች ሆነው የሚያገለግሉ በመሆኑ ለክልሉ ወይም ለዞን ከተማው የተመደበው የቀን ውሎ አበል ተመን ለወረዳ ከተማው ጭምር የሚያገለግል ይሆናል፡፡
9. የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የማእከላዊ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የብዝሀ ከተማ መርህ የሚከተሉ ስለሆነ የክልል ዋና ከተማ ቢሮዎች ያሉባቸዉ ከተሞች ተወስደዉ ለልክሎቹ ዋና ከተማ የተወሰነዉ የአበል መጠን ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
9. አዲስ የክልል/ዞን/ወረዳ/ከተማ ሲሰየም ወይም ሲከፈት የክልል መንግሥታት ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 7. የአየር ጠባይ አበል ወደ ሚከፈልበት የሥራ ቦታ ለሚላክ ተሿሚ የሚከፈል የቀን ውሎ አበል

አንድ የመንግስት ተሿሚ ለሥራ ጉዳይ የአየር ጠባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ ሲሄድ፣

ሀ/ በአንደኛ ደረጃ የተመደበ ማለትም የደመወዙ 40% የአየር ጠባይ አበል የሚከፈልበት የሥራ ቦታ ከሆነ የውሎ አበሉ 40%፣

ለ/ በሁለተኛ ደረጃ የተመደበ ማለትም የደመወዙ 30% የአየር ጠባይ አበል የሚከፈልበት የሥራ ቦታ ከሆነ የውሎ አበሉ 30%፣

ሐ/ ሦስተኛ ደረጃ የተመደበ ማለትም የደመወዙ 20% የአየር ጠባይ አበል የሚከፈልበት የሥራ ቦታ ከሆነ የውሎ አበሉ 20% በተጨማሪ ታክሎ ይከፈለዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 8. ስለተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ ቀደም በነሐሴ 24 ቀን 2005 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ሲሰሚ/ሚጼ3/127/05 እና በየካቲት 01 ቀን 2008 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ፐ.ሰ.ሚ ጠ30/ጠ13/1052 ተላልፈው በሥራ ላይ ያሉት የመንግስት ተሿሚዎች የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

### 9. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያው እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው በኮሚሽኑ እየታየ በጥናት ላይ ተመስርቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 10. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበና በተቋሙ ድረገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ መስከረም 2018**

**መኩሪያ ኃይሌ (ዶ/ር)**
**የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር**